በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

# መመሪያ ቁጥር፡ 1113/2018

# የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናል ግምገማ እና እውቅና አሰጣጥ መመሪያ

# Directive No: 1113/2025

# Directive for the Evaluation and Accreditation of Local Research Journals

**ጥቅምት፣ ፪ሺ፲፰ ዓ.ም/October, 2025**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ/Addis Ababa, Ethiopia**

**ትምህርት ሚኒስቴር /Ministry of Education**

## የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናል ግምገማ እና እውቅና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1113/2018

### መቅድም

የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎችን ታይነት፣ ጥራትና ተፅእኖ ለማሳደግ እና ዓለም አቀፍ የአቻ ግምገማ ደረጃዎችን፣ የአርትዖት ግልጽነት እና የሥነ-ምግባራዊ ኅትመቶችን መከተላቸውን የሚያረጋግጥ ማዕቀፍ የማዘጋጀት አስፈላጊነት እያደገ መምጣቱ፣

በሃገር ውስጥ ቋንቋዎች ለሚታተሙ የምርምር ጆርናሎች ዕውቅና ለመስጠትና ለመደገፍ የሚያስችል ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ጥራት ያላቸው የምርምር ጆርናሎች ተዘጋጅተው ተደራሽ እንዲሆኑ የጥራት ቁጥጥር ማድረግ ማስፈለጉ፣ እንዲሁም ጆርናሎች ለማህበረሰቡ ማበርከት ያለባቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ለማድረግ የሚያስችል የጆርናል እውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ማዘጋጀት ማስፈለጉ፣

ስለዚህ ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፶፪/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፺፫(፪) እና አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬፣ አንቀጽ ፴፬ (መ እና ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን የሃገር ውስጥ የምርምር ጆርናሎች ግምገማ እና እውቅና አሰጣጥ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## Directive for Evaluation and Accreditation of Local Research Journals (Directive No. 1113/2025)

### Preamble

WHEREAS, there is a growing demand to enhance the visibility, quality, and impact of local research journals, necessitating a framework that ensures their adherence to international standards of peer review, editorial transparency, and ethical publishing;

WHEREAS, there is a critical need to provide a framework for recognizing and supporting local research journals published in national languages;

WHEREAS, the need for quality control to ensure that quality research journals are produced and accessible, as well as the need to develop a journal accreditation system to ensure that journals contribute to ተሀ society as they should;

NOW, THEREFORE, as per the Higher Education Proclamation No.1152/2019, Article 92(5), and Proclamation No. 1263/2021, Article 34 (D and E), the Ministry of Education hereby issued a directive for the evaluation and accreditation of local research journals.

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የሀገር ውስጥ የምርምር ጆርናል ግምገማ እና እውቅና አሰጣጥ መመሪያ፣ መመሪያ ቁጥር** 1113/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የማያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱት ቃላት እና ሀረጎች የሚከተሉት ትርጉሞች ይኖራቸዋል፦

፩/. **"ዕውቅና ሰጪ"** ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን፣ የሃገር ውስጥ የምርምር ጆርናል ምዘናና የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓትን የመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው።

፪/. **"የአማካሪ ቦርድ"** ማለት በምርምር ጆርናል መሻሻል ላይ አስገዳጅ ያልሆነ ስልታዊ ምክር የሚሰጥ በጆርናል ወሰን ውስጥ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ስብስብ ነው። የአማካሪ ቦርድ አባላት የጋራ መድረክ ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል። ለምርምር ጆርናል ሙያዊ ምክር፣ ተዓማኒነት እና ድጋፍ የሚሰጥ የታወቁ ባለሙያዎች ቡድን ነው።

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

**Article 1. Short Title**

This Directive may be cited as **"Directive for Evaluation and Accreditation of local Journals, directive No. 1113/2025."**

**Article 2: Definitions**

Unless the context otherwise requires, the terms and phrases in this directive shall have the following meanings:

1/. **"Accreditor"** means the Ministry of Education, w hich is mandated to oversee the national journals evaluation and accreditation system.

2/. **"Advisory Board"** shall mean a group of accomplished professionals with expertise in the scope of a journal that provides non-binding strategic advice on the betterment of the journal. Members of the Advisory Board may or may not have a common forum. It is a group of recognized experts who provide guidance, credibility, and support to an research journal.

፫/. **“የፀረ-ስርቆት ፍተሻ/ማጣራት”**:- ማለት የምርምር ጆርናል ጽሑፍን /መጣጥፍ/ በተለያየ የኦንላይን ዳታቤዝ ይዘት ጋር ስለመወሰዱ የማነጻጸር ሂደት ነው። አንድ ጽሑፍ/መረጃ ያለ ተገቢ እውቅና ከሌሎች ምንጮች የተገለበጡ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ልዩ ሶፍትዌር ወይም መሳሪያዎችን በመጠቀም የመፈተሽ ሂደት ነው።

3/. **“Anti-plagiarism checking”:** shall mean the procedure of scanning a research journal/article/ text against vast databases of online content for its originality test. It is the process of using specialized software or tools to detect whether a piece of writing contains content copied from other sources without proper acknowledgment.

፬/. **“ማህበር”** ማለት የኢትዮጵያ ምርምር ጆርናል አርታኢዎች ማህበር (ERJEA) ማለት ነው።

4/. **“Association”** shall mean the Ethiopian Research Journal Editor’s Association (ERJEA).

፭/. **“የአርታኢዎች ቦርድ”** ማለት ጆርናሉ በሚታተምበት ዘርፍ ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው ታዋቂ ባለሙያዎች ስብስብ ሲሆን የምርምር ጽሑፍን ለማረጋገጥ፣ ለመምረጥ፣ ለማተም እና ለማሰራጨት የበላይ ጠባቂ ሆኖ የሚያገለግል፣ እንዲሁም የጆርናሉን አቅጣጫ የሚመራ፣ የታተመውን ስራ ጥራት የሚያረጋግጥ እና የአካዳሚክ ደረጃዎችን የሚያስከብር አካል ነው።

5/. **"Editorial Board"** shall mean a group of prominent professionals with expertise in the discipline areas of the journal that serves as a gatekeeper for the validation, selection, publication, and dissemination, as well as guides the journal’s direction, ensures the quality of published work, and uphold academic standards.

፮/. **“ሥነ-ምግባራዊ ህትመት”**:- በህትመት ሂደት ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች በከፍተኛ ኃላፊነት እና መልካም ስነ-ምግባርን በመላበስ፣ ጥናትና ምርምሮች ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲሰራጩ፣ ተገቢው እውቅና እንዲያገኙ እና የሳይንሳዊ ዘገባ ትክክለኛነት እንዲጠበቅ የማድረግ ሂደት ነው።

6/. “**Ethical Publishing”:** shall mean the responsible and honest conduct of all participants in the publication process, ensuring that research is reported transparently, credit is given appropriately, and the integrity of the scientific record is maintained.

፯/. **“ገምጋሚ”** ማለት በሃገር ውስጥ የምርምር ጆርናል ምዘናና ዕውቅና አሰጣጥ መስፈርት መሰረት የሀገር አቀፍ ጆርናልን ጥራት እንዲገመግም በትምህርት ሚኒስቴር የተመረጠ የባለሙያዎች ወይም ተመራማሪዎች ቡድን ነው፡፡

፰/ **“ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ መለያ ቁጥር (ISSN)”** ማለት እንደ መጽሔቶች፣ ጆርናሎች፣ ጋዜጦች እና ብሎጎች ያሉ ተከታታይ ህትመቶችን ለመለየት የሚያገለግል ልዩ፣ ደረጃውን የጠበቀ ባለ ስምንት አሃዝ ኮድ ነው፡፡

፱/ **"ጆርናል"** ማለት በዓመት በውስን ጉዳዮች ላይ አተኩሮ በምርምር የተገኙ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ሪፖርት ለማድረግ በየጊዜው የሚታተም ሳይንሳዊ የምርምር ሰነድ ነው፡፡ መረጃን፣ ሃሳቦችን እና ምርምርን ለመለዋወጥ እንደ ቁልፍ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል የህትመት ወይም የጽሁፍ ዘገባ ነው፡፡

፲/. **“ሚኒስቴር”** ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ማለት ነው፡፡

፲፩/. **“ስርቆት”** ማለት የሌላ ሰውን ትክክለኛ ሃሳብ፣ ጽሑፍ፣ ዳታ እና ሌሎች የፈጠራ ስራዎችን መቅዳት እና የሌሎችን የምርምር ስራ ያለ በቂ እውቅና እንደ ራስ ውጤት አድርጎ ማቅረብ ማለት ነው፡፡ ስርቆት በአካዳሚክ እና በምርምር ላይ ያለ ከባድ የስነ-ምግባር ጥሰት ሲሆን የሌላ ሰውን ቃላት፣ ሃሳቦች፣ መረጃዎች፣ ጽሁፍ ወይም

7/. **"Evaluator"** means any group of professionals, or pool of experienced researchers who are assigned by the Ministry to assess the quality of a national journal as per the criteria established in the Ministry's Directive for local Journal Evaluation.

8/ **“An International Standard Serial Number (ISSN)”** shall mean a unique, standardized eight-digit code used to identify serial publications, such as magazines, journals, newspapers, and blogs

9/. **"Journal"** shall mean a scientific, research document that is published periodically with a specified number of issues per year, aimed at reporting scientific findings from research. It is a publication or written record that serves as a key tool for sharing information, ideas, and research.

10/. **"Ministry"** shall mean the Ministry of Education.

11/. **"Plagiarism"** shall mean copying of the exact idea, text, data, and other creative work of another person and presenting it as the original result of own research work, without proper citation. Plagiarism is a serious ethical violation in academia and research that involves using someone else’s words, ideas, data, text, or intellectual work without proper

ምሁራዊ ስራዎች ያለ በቂ እውቅና መጠቀምን ያካትታል።

acknowledgment, presenting them as one's own.

፲፪/. **"ምስለ-ጆርናል"፡-** ማለት የምርምር ጆርናሎችን ያለ አቻ የግምገማ ሂደት በክፍያ በፍጥነት የሚያትም የሃሰት ጆርናል ሲሆን በተጭበረበረ መንገድ ከደራሲያን የሕትመት ገንዘብ ለመሰብሰብ ብቻ ሲባል ጥራትን በማበላሸት የሚቋቋም ጆርናል ነው። ምስለ-ጆርናል አብዛኛውን ጊዜ ከአካዳሚክ ተዓማኒነት ይልቅ ትርፍ የሚያስቀድም፣ ተገቢው የአቻ-ግምገማ ስርዓት የሌለው እና ደራሲያንን እና አንባቢዎችን የሚያሳስት ጆርናል ነው።

**12/. "Predatory Journals":** shall mean a pseudo-journal that rapidly publishes research manuscripts without subjecting them to a peer-review process at the cost of compromising scientific quality, merely for collecting fees for publication from authors as a bogus money-making scheme. Predatory journals are publications that often prioritize profit over academic integrity, lack proper peer review, and mislead authors and readers.

፲፫/. **"ዳግም ዕውቅና መስጠት" ፡-** ማለት አንድ እውቅና ያገኘ የምርምር ጆርናል የዕውቅና ጊዜው የሚያበቃበት ቀን ላይ በመመርኮዝ እንደገና ገምግሞ እውቅና የመስጠት ሂደት ነው። አንድ ጆርናል እውቅናውን ለማሳደስ፣ የተቀመጡ የጥራት፣ የአስተዳደር እና የይዘት ደረጃዎችን ማሟላቱን እና ማስቀጠሉ የሚረጋገጥበት መደበኛ ሂደት ነው።

**13/. "Reaccreditation"** shall mean the re-evaluation and re-accrediting of a research journal based on the expiry date of the accreditation. It is a formal process where a journal undergoes evaluation to renew its accredited status, ensuring it continues to meet established standards of quality, management, and content.

## አንቀጽ ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚታተሙ፣ ለእውቅና እና ለዳግም እውቅና በሚያመለክቱ የምርምር ጆርናሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። እንዲሁም በሌሎች ተቋማትና ማህበራት የሚታተሙ የምርምር ጆርናሎች ለዕውቅና ሊያመለክቱ ይችላሉ።

## Article 3. Scope of Application

This directive shall be applicable for evaluating, accrediting, and re-accrediting all research journals published in higher education institutions of Ethiopia. Research journals published by other institutions and associations may also apply for accreditation.

## ክፍል ሁለት

## ማመልከቻ፣ መስፈርቶች፣ ግምገማ እና እውቅና

### አንቀፅ ፬. የጆርናል ግምገማ እና እውቅና አሰጣጥ ሂደት

በምርምር ጆርናል ግምገማ እና እውቅና ሂደት ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ተግባራት በሚከተለው መርሃ-ግብር መሰረት ይከናወናሉ፡-

**፩/.** ሚኒስቴሩ ለጆርናል እውቅና የማመልቻ ጥሪ ያደርጋል:: (5 ቀናት)

**፪/.** የጆርናሎች ዋና አዘጋጆች ማመልከቻቸውን በቀረበው መስፈርት መሰረት ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ:: (20 ቀናት)

**፫/.** ሚኒስቴሩ ማመልከቻውን እና አስፈላጊ የሆኑ የጆርናሉ ሰነዶች ስለመሟላታቸው በማጣራት ለገምጋሚው ያስተላልፋል:: (5 ቀናት)

**፬/.** ገምጋሚው ለግምገማው ብቁ የሆኑ ጆርናሎችን ይገመግማል:: (30 ቀናት)

**፭/.** ገምጋሚው የግምገማ ሪፖርቱን አጠናቅሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል:: (10 ቀናት)

**፮/.** ሚኒስቴሩ የገምጋሚውን ሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳቦችን ይገመግማል፣ እውቅና የተሰጣቸውን መጽሔቶች ዝርዝር ያሳውቃል፣ እንዲሁም ውጤቱን

## PART TWO

## APPLICATION, REQUIREMENTS, EVALUATION, AND ACCREDITATION

### Article 4. Processes of Journal Evaluation and Accreditation

The major activities in the journal evaluation and accreditation process shall take place per the following schedule:

**1/.** The Ministry issues a call for journals to apply for accreditation. (5 days)

**2/.** Editors-in-Chief of journals submit to the Ministry their applications per the submission requirements. (20 days)

**3/.** The Ministry checks the completeness of the application information and required documents of journals and forwards the same to the Evaluator. (5 days)

**4/.** The Evaluator evaluates eligible journals. (30 days)

**5/.** The Evaluator compiles and writes the review report and submits it to the Ministry. (10 days)

**6/.** The Ministry reviews the Evaluator's report and recommendations, announces the list of accredited journals, and communicates to the applicant journal. (10 days)

ለአመልካቹ ጆርናል ያስተላልፋል:: (10 ቀናት)

፯/. ሚኒስቴሩ ቅሬታን ይቀበላል:: (5 ቀናት)

7/. The ministry accepts appeals. (5 days)

፰/. ሚኒስቴሩ ሁሉንም ቅሬታዎች እና ይግባኞች እንደገና ይገመግማል:: (5 ቀናት)

8/. The Ministry re-evaluates all grievances and appeals. (5 days)

፱/. ሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጣቸውን ጆርናሎች ዝርዝር ለአካዳሚክ ማህበረሰብ/ሕዝብ ይፋ ያደርጋል:: (7 ቀናት)

9/. The Ministry announces the list of accredited journals to the academic community/public. (7 days)

፲/. እንደአስፈላጊነቱ የግምገማው መርሐ-ግብር በአመት ሁለት ጊዜ ሊደረግ ይችላል::

10/. Conditional adjustments may also be made on the evaluation period to allow for biannual scheduling.

## አንቀጽ ፭. ከማመልከቻ ጋር መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች

## Article 5. Documents to be submitted with the application

ከጆርናል የዕውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት ማስረጃዎች መቅረብ አለባቸው:-

The following documents must be submitted with the journal accreditation application:

፩/. በዋና አርታዒው የተፈረመ የማመልከቻ ደብዳቤ;

1/. A letter of application signed by the Editor-in-Chief;

፪/. ለመመዝገቢያ እና እውቅና ማረጋገጫ (የምዝገባ እና የእውቅና ደብዳቤ ወይም እንደገና እውቅና ማረጋገጫ)

2/. Evidence for registration and accreditation (a letter of registration and accreditation or reaccreditation)

፫/. ስለ ጆርናሉ ገላጭ መረጃ (በጆርናሉ ቅጂዎች ውስጥ ካልተካተተ) ከደጋፊ ሰነዶች ጋር ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል:: እነዚህም:-

(ሀ). የአታሚው እና/ወይም የጆርናል ባለቤት ስም፣ እና ዝርዝር አድራሻው፣

(ለ). የህትመት ብዛት በአመት፣

3/. Descriptive information about the journal (if not included in the journal copies), together with supportive documents need to be submitted. These include:

(A). Name of the publisher and/or owner, its address, and contact details

(B). Publishing frequency in a year

(ሐ). የህትመት መርሐ-ግብር፣

(C). Publishing schedule

(መ). ጆርናሉ ቢያንስ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ሳይቆራረጥ ስለማሳተሙ የሚያሳይ ማስረጃ፣

(D). Evidence that exhibits the journal has been published for a minimum of three consecutive years uninterruptedly.

(ሠ). ዓለማቀፍ ስታንዳርድ መለያ ቁጥር (አይ.ኤስ.ኤስ.ኤን፣ ኢ-አይ.ኤስ.ኤስ.ኤን (በኦንላይን ከሆነ)፣

(E). International Standard Serial Number (ISSN, e-ISSN (if online))

(ረ). የጆርናል አዘጋጁን የድረ-ገፅ መገኛ የሚያሳይ አድራሻ (ዩ.አር.ኤል.)፣

(F). Uniform Resource Locator (URL) for the journal website of the host

(ሰ). የሃርድ ቅጂ ህትመት ብቻ ያላቸው ጆርናሎች ባለፉት ሶስት አመታት የታተሙትን የእያንዳንዱን እትም ሁለት የህትመት ቅጂዎች ከሶፍት ቅጂዎች ጋር ስርቆትን ለማጣራት እንዲቻል ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል::

(G). Print-only journals are required to submit two print copies of each Issue of the Journal published in the last three years, along with soft copies for plagiarism checking.

(ሸ). የጆርናል ኢሜል፣ ፖስታ እና የቢሮ አድራሻዎች፣

(H). Journal email, postal, and physical addresses

(ቀ). በታዋቂ ዓለም አቀፍ ጥራት ጠቋሚ ላይ የቅርብ ጊዜ ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ስለመሆኑ (በማመልከቻ ጊዜ በስራ ላይ ያለ) ወይም የሚመዘግብ ዳታቤዝ ካለ (ርዕሶች እና አታሚዎች በዝርዝር) ሊካተቱ ይገባል::

(I). List the latest (active during application) reputable international indexing or abstracting databases, if any (titles and publishers required)

(በ). የአርትዖት ፖሊሲዎች፣

(J) Editorial policies

(ተ). የጽሁፍ ማቅረቢያ መንገድ እና ዘይቤ፣ ወይም "ለደራሲያን የተዘጋጀ ጋይድላይን"፣

(K). Submission and style, or "Guideline to authors"

(ቸ). የሕትመት ዘዴ (በኦንላይን፣ በወረቀት ህትመት ብቻ፣ ወይም የሁለቱ ጥምር) ስለመሆኑ፣

(ኀ). በደንበኝነት ላይ የተመሰረተ ወይም ለሁሉም ተደራሽ ስለመሆኑ፣

(ነ). ለሁሉም ተደራሽ ካልሆነ፣ በእያንዳንዱ ባለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ የነበረው የስርጭት መጠን (በራሱ ተቋም ወይም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ፣ ከተቋሙ ውጪ ግን በአገር ውስጥ፣ ወይም ከአገር ውጭ) ስለመሆኑ፣

(ኘ). ለሁሉም ተደራሽ ከሆነ፣ ሙሉ ጽሑፉ የተጫነበት መርሐ-ግብር (ከተቻለ ላለፉት ሶስት ዓመታት የታተሙ እትሞች መዝገብ) ማቅረብ፣

(አ). ጆርናሉ ለድህረ-ምረቃ ምርምር ምቹ መድረክ ሆኖ የሚያገለግል ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ (የትኞቹ ጽሁፎች ወይም አበርክቶዎች ከድህረ-ምረቃ እንደሆኑ መለየት)፣

(ኸ). የአርታኢዎች እና አማካሪዎች አካዳሚክ ደረጃ፣ የስራ ቦታቸው፣ እና ብቃታቸው፣ ሳይንሳዊ ህትመቶች፣ ተቋማዊ ግንኙነት እና የእያንዳንዳቸው አጭር የህይወት ታሪክ፣ እና ሀገራዊ እና/ወይም አለም አቀፍ ሳይንሳዊ ቁመናቸውን የሚያሳዩ ማቅረብ ያስፈልጋል::

(L). Publishing medium (whether online, print only, or combined)

(M). Subscription-based or Open Access

(N). If not Open Access, distribution size (total within the mother institution [e.g., university], total outside the institution but within the country, total outside the country) during each of the last three years

(O). If Open Access, full-text uploading schedule (if possible, record for each of the last three years' published issues)

(P). Information on whether the journal serves as a platform for graduate research (identify which articles or contributions are such products)

(Q). Full names of editorial and advisory council members, along with their academic ranks, or job positions, and qualifications, scholarly publications, institutional affiliation, plus short bios of each of them demonstrating their national and/or international scholarly stature

**አንቀጽ ፮. ጆርናል ለግምገማ ብቁ እንዳይሆን የሚያደርጉ ሁኔታዎች (የልየታ/የቅድመ-ግምገማ ደረጃ)፣**

**Article 6. Conditions that make a journal ineligible for review (Triage/pre-evaluation stage)**

በልየታ ወይም በቅድመ-ግምገማ ወቅት አንድ ጆርናል ለግምገማ ብቁ እንዳይሆን የሚያደርጉ ሁኔታዎች፣

Circumstances that may make a journal ineligible for evaluation, at a triage or pre-evaluation phase, include:

፩/. ጆርናሉ በተቋቋመበት ወቅት በትምህርት ሚኒስቴር ካልተመዘገበ፣

1/. If the journal was not registered with the Ministry of Education at the time of its establishment,

፪/. የጆርናሉ ህትመት ባለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት መቆራረጥ ካሳየ፣

2/. If the journal's publication has been interrupted for the past three consecutive years,

፫/. ጆርናሉ በዓመት ለማሳተም ካቀዳቸው መድብሎች ውስጥ በማንኛውም ምክንያት ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ በተባለው ጊዜ ውስጥ ማሳተም ካልቻለ፣

3/. If the journal has been unable to publish any of the issues it plans to publish annually within the stated time frame for any reason in the past three years,

፬/. የአቻ ግምገማ ሂደትን ጨምሮ የተጠቃለለ የጥራት ቁጥጥር ሪፖርት አያይዞ ማቅረብ ካልቻለ፣

4/. If it fails to submit a comprehensive quality control report including the peer review process,

፭/. በቅድመ-ማመልከቻም ሆነ በልየታ ምርመራ ወቅት በጸረ-ስርቆት ምርመራ ከ፳% በላይ የስርቆት ጽሁፍ ያለው ጆርናል ከሆነ፣

5/. If the journal has a plagiarism rate of above 20% during the pre-application or triage process,

፮/. ያልተሟላ ማመልከቻ የቀረበ ከሆነ፣

6/. If an incomplete application is submitted,

፯/ ወሰኑ ከሳይንሳዊ ጆርናል ህትመት ውጪ ከሆነ፣

7/ If the decision is outside the scope of scientific journal publication,

፰/. የጸረ-ስርቆት ምርመራን በተመለከተ

8/ Concerning Anti-Plagiarism Detection

(ሀ) ሁሉም የጆርናል መድብሎች ጸረ-ስርቆት መመርመሪያ ሶፍትዌርን በመጠቀም ከስርቆት የጸዳ ስለመሆኑ በትምህርት ሚኒስቴር

(A). All journal submissions must be re-checked by the Ministry of Education for plagiarism using anti-plagiarism detection software.

አማካኝነት በድጋሚ መፈተሸ ይኖርበታል። በዚህም መሰረት ለዕውቅና ወይም ለድጋሚ እውቅና ያመለከተው ጆርናል ያስመዘገበው አማካይ የስርቆት ጽሁፍ መጠን፡-

(i) ፳% እና ከዚያ በታች ከሆነ - ለግምገማ ብቁ ይሆናል፣

(ii) ከ፳% በላይ ከሆነ - ጆርናሉ ከግምገማ ሂደቱ ውጪ ይሆናል።

(ለ) ጆርናሉ በራሱ መንገድ ስርቆት መጠኑን አጣርቶ ሪፖርቱን እንዲያቀርብ የሚመከር ቢሆንም ለመጨረሻ ውሳኔ ጥቅም ላይ የሚውለው አማካይ የስርቆት ጽሁፍ መጠን በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተሰልቶ የሚቀርበው ነጥብ ነው።

**አንቀፅ ፯. የግምገማ መስፈርቶች እና ለእውቅና የተሰጡ ነጥቦች**

በጆርናል ማመልከቻ ግምገማ ወቅት የሚከተሉት መመዘኛዎች ከተሰጣቸው ነጥቦች ጋር ወጥ በሆነ መልኩ መተግበር አለባቸው፡-

**፩/. የምርምር ጽሁፎች ሳይንሳዊ ጥራት** (፶ ነጥቦች)

(ሀ) ዋና ቅጂ እና ከስርቆት ነፃ ስለመሆኑ፣ የተሟሉ እና የቅርብ-ጊዜ ማጣቀሻዎች ስለመጠቀሙ፣

(ለ) የቋንቋ ጥራት እና ብቃት፣ በውስጥ እና የዋቢ መጻህፍትን በአግባቡ ስለመጠቀሙ፣

(ሐ) አብስትራክት እና ቁልፍ ቃላትን በትክክል ስለመፃፉ፣

Accordingly, the average plagiarism rate recorded by a journal applying for accreditation or re-accreditation is:

(i). If it is 20% or less - it will be eligible for review,

(ii) If it is more than 20% - the journal will be excluded from the review process.

(B) Although it is recommended that the journal itself investigate the plagiarism rate and submit its report, the average plagiarism rate used for the final decision is the score calculated and provided by the Ministry of Education.

**Article 7. Evaluation Criteria and Points Allotted for Accreditation**

The following criteria, along with the allocated points, shall be uniformly applied in the external evaluation of applicant journals:

1/. **Scholarly quality of research articles** (50 pts)

(A) Originality and freedom from plagiarism, complete and up-to-date references;

(B) Language quality and proficiency, proper use of in-text and bibliography citations,

(C) Proper write-up of the abstract and keywords,

(መ) መግቢያውን በትክክልና በአግባቡ ስለመፃፉ፣

(ሠ) የጥናቱ ዘዴ፣ ውጤት፣ ትንተና፣ መደምደሚያ፣ እና ምስጋና በአግባቡ ስለመፃፉ፣

(ሸ) በጆርናሉ ዘይቤ እና መስፈርት መሰረት ስለመዘጋጀቱ

(ቀ) የጸረ-ስርቆት መፈተሻ ሶፍትዌር አይነት በወጥነት ለመጠቀም እና ወቅታዊነቱ መገለጽ አለበት።

(ተ) የማግለል መስፈርት የሚወሰነው በባለሙያዎቹ ነው።

(ቸ) በታተሙ ጆርናሎች ውስጥ የተካተቱት ጽሑፎች ዋና ቅጂ ስለመሆናቸው የማረጋገጥ ሃላፊነትን ስለሚወስደው አካል መወሰን አስፈላጊ ነው።

**፪/. የጆርናሉ ጥራት እና ጽሁፉ ከጆርናሉ ወሰን ጋር የሚኖረው አግባብነት (፲ ነጥቦች)**

(ሀ). ደረጃውን የጠበቀ የሽፋን ዲዛይን ስለመጠቀሙ፣

(ለ). የፅሁፎቹ ቅርጽ፣ አቀማመጥ፣ አይነት እና መጠን አንድ አይነትነት፣

(ሐ). ትክክለኛ የማሳያዎች አጠቃቀም፣ የጽሁፎች አይነቶች እና ከጆርናሉ ወሰን ጋር ስለመጣጣማቸው፣

**፫/. የአርታዒ ቦርድ አባላት ሳይንሳዊ አበርክቶ መገለጫ** (፲ ነጥቦች)

(D). Proper write-up of introduction,

(E) Proper write up of methodology, results, discussions, conclusions, and use of acknowledgements,

(F) The write up is as per the journal style and requirement.

(G) The type of anti-plagiarism checking software shall be specified for its consistent application and timeliness.

(H) Exclusion criteria shall be decided by the professionals

(I) It is essential to stipulate who to check the originality of articles in the published journals

**2/. Quality of copy-editing and alignment of articles with the scope of the journal** (10 pts)

(A). Utilization of professional cover design,

(B). Uniformity of format, text layout, font type, and size,

(C). Proper use of illustrations, types of articles, and their alignment with the scope of the journal,

**3/. Editorial Board members' scholarly profile** (10 pts)

(ሀ). የአርታዒ ቦርድ አባላት ሙሉ ስማቸው ዝርዝር እና ተቋማዊ ቁርኝታቸው ስለመካተቱ፣

(A). Presence of a list of Editorial Board members with their full names and institutional affiliation,

(ለ). የአርታዒዎች ትምህርት ደረጃ፣ የምርምር መጣጥፎች ብዛት፣ በሌሎች ታዋቂ ሀገራዊ እና አለምአቀፍ መጽሔቶች ላይ ስላላቸው አበርክቶ፣

(B). Qualification, and rank of editors, number of research articles in other reputable national and international journals,

(ሐ). የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት ስፔሻላይዜሽን ከጆርናሉ የትኩረት መስኮች ጋር ያለው አግባብነት

(C). The relevance of the field of specialization to the journal's focus areas,

(መ). በምስለ-ጆርናሎች ውስጥ አለመሳተማቸው፣

(D). Absence from publishing in predatory journals

**፬/. የአማካሪ ቦርድ አባላት ሳይንሳዊ አበርክቶ መገለጫ** (፭ ነጥቦች)

**4/. Advisory Board members' scholarly profile** (5 pts)

(ሀ). የአማካሪ ቦርድ አባላት ሙሉ ስማቸው ዝርዝር እና ተቋማዊ ቁርኝታቸው ስለመካተቱ፣

(A). Including the full names and institutional affiliations of the members of the Advisory Board,

(ለ). የአማካሪ ቦርድ አባላት ብቃት እና ደረጃ፣ ስብጥር እና አካታችነት (በዲሲፕሊን፣ በተቋም፣ በጾታ እና በጂኦግራፊ) ፣

(B). Advisory Board members' qualification and rank composition and diversity (disciplinary, institutional, gender & geographic),

(ሐ). የአማካሪ ቦርድ አባላት የምርምር መጣጥፎች ብዛት በሌሎች ታዋቂ የሀገር እና አለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ ያላቸው ህትመት፣

(C) Number of research articlesAdvisory by Board members in other reputable national and international journals,

**፭/. በአንድ እትም ሊኖር ስለሚገባ የጽሑፍ ብዛት እና ስብጥር** (፲ ነጥቦች)

**5/. Number and diversity of articles per issue** (10 pts)

(ሀ). በአንድ እትም ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ዝቅተኛው የጽሑፎች ብዛት እንደሚከተለው ነው፡-

(i)_ በዓመት ሁለት ጊዜ እና በላይ ለሚያሳትም ጆርናል - በእያንዳንዱ እትም ውስጥ ቢያንስ ፭ ጽሑፎችን፣ እንዲሁም

(ii)_ በአመት አንድ ጊዜ የሚያሳትም ጆርናል - ቢያንስ ፲ ጽሑፎችን ሊያካትት ይገባል።

(A). The minimum number of articles that should be included in an issue is as follows:

(i)_ For biannual journals or above - a minimum of 5 articles per issue, and

(ii)_ For annual journals - a minimum of 10 articles per issue shall be included.

(ለ). የጆርናል የጽሁፍ ጥንቅርን በተመለከተ፡- ቢያንስ ፸ በመቶ የሚሆኑት ጽሁፎች ዋና ቅጂ የምርምር ስለመሆናቸው፣

(B). Regarding Journal Composition: a minimum of 70% of all published content are dedicated to original research articles,

(ሐ). የጽሑፎች መልከዓ-ምድራዊ እና ተቋማዊ ስብጥር (ስለ ጸሃፊዎች አድራሻ እና ማስታወሻዎች እንደተመላከተው) ፣ በብዝሃ-ዘርፍ ጆርናሎች ውስጥ ያሉ ጽሑፎች ብዝሀ-መስክ ስለመሆናቸው፣

(C). Geographic and institutional origin of articles (as indicated in addresses of authors and notes about authors), subject diversity of articles in multidisciplinary journals,

(መ). ብዝሃ-ይዘት ያላቸው ጽሁፎች (ግምገማዊ ጽሁፎች፣ ለአርታዒው መልዕክት፣ አጫጭር ሳይንሳዊ ማስታወሻዎች፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ጽሁፎች፣ ወዘተ) ስለመካተታቸው፣

(D). Inclusion of diversified types of articles (review papers, letter to the editor, short notes, short communications release of technologies, etc) per issue,

(ሠ). በአንቀጽ 7(5)(ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠቀሱት ሌሎች የጽሑፍ ዓይነቶች በማይኖሩበት ጊዜ ለዋና ቅጂ የምርምር ጽሑፎች ቅድሚያ ይሰጣል። ስለዚህ በውስጡ 100% ዋና ቅጂ ጽሑፍ የያዘ እትም (ብዝሃ-ይዘት ያላቸው ጽሁፎችን

(E). Subject to the provisions of Article 7(5)(b), original research articles shall be given priority in the absence of other types of articles mentioned above. Therefore, a publication that is of 100% original articles

ባያካትትም እንኳ) ከፍተኛውን ነጥብ ያገኛል::

(even if it does not include multi-content articles) shall receive the highest score.

**፮/. የአርትዖት ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች** (፭ ነጥቦች)

***6/. Editorial policies and Directives*** *(5 pts)*

(ሀ) ለጸሃፊዎች የአሰራር መመሪያ መኖሩ እና ግልጽነት፣

(A) Presence and clarity of Directives for authors,

(ለ) የአቻ ግምገማ ፖሊሲ እና ሌላ የአርትዖት ፖሊሲዎች (የፍላጎት ግጭት፣ የስነምግባር ፖሊሲ፣ የመሻር ፖሊሲ፣ የቅጂ መብት ፖሊሲ፣ የጸረ-ስርቆት ፖሊሲ እና ሌሎችም) ስለመኖራቸው እና ግልጽነታቸው፣

(B) Presence and clarity of peer review policy, other editorial policy (conflict of interest policy, ethical policy, retraction policy, copyright policy, plagiarism policy and others).

**፯/. የጆርናል ስርጭት እና የሙሉ ጽሑፍ ተደራሽነት** (፭ ነጥቦች)

**7/. Distribution of journal and mode of access to full text** (5 pts)

(ሀ). የህትመት መደበኛነት፣

(A) Regularity of publication,

(ለ). የድረ-ገጽ ጥራት፣

(B) Website quality,

(ሐ). ለሁሉም ተደራሽ መሆኑ ወይም በሃርድ ኮፒ ብቻ የሚዘጋጅ ስለመሆኑ፣

(C) Open Access, or Print only

**፰/. በሌሎች ዓለም አቀፍ የጆርናል ጥራት ጠቋሚ ቋቶች ውስጥ ስለመመዝገቡ (ዌብ ኦፍ ሳይንስን እና/ወይም ስኮፐስን ሳያካትት)** (፭ ነጥቦች)

**8/. Registration in other international indexing databases (other than Web of Science and/or Scopus)** (5 pts)

(ሀ). ከዌብ ኦፍ ሳይንስ እና/ወይም ከስኮፐስ ውጪ በሌሎች የጆርናል ጥራት ጠቋሚ ቋቶች ውስጥ ስለመመዝገቡ፣

(A) Registration in indexing databases other than Web of Science, and/or Scopus;

(ለ). የጽሁፍ መለያዎች (DOI)፣ URL ያለው ስለመሆኑ፣

(B) Article identifiers (DOI), URL

## አንቀፅ ፰. የነጥብ አሰጣጥ

፩/. ገምጋሚው የነጥብ አሰጣጥ ሂደቱን በተቻለ መጠን ተጨባጭ ለማድረግ ለእያንዳንዱ መስፈርት የተመደቡትን አጠቃላይ ነጥቦች በጠቋሚዎች መሰረት ተጨማሪ ዝርዝር ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

፪/. ገምጋሚው በግምገማ ውስጥ በእያንዳንዱ መስፈርት መሰረት ነጥቦችን የማስቀመጥ ሃላፊነት የሚኖርበት ሲሆን ውጤቶቹ ያላግባብ ወይም በዘፈቀደ ያልተሞሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ ትክክለኛ ማረጋገጫዎችን ይሰጣል፣ ማስረጃዎቹ ማንኛውም አይነት ቅሬታ በሚቀርብበት ጊዜ እንደገና የሚታዩ ይሆናል፡፡

፫/. በየእትም የሚገመገሙ መጣጥፎችን ከመረጠ በኋላ የገምጋሚው ቡድን ሰብሳቢ እያንዳንዱን ዕትም ለገምጋሚዎች በነፍስ ወከፍ ለበለጠ ግምገማ ይደለድላል፡፡

፬/. በ ፯.፩ ላይ በተገለጹት ድንጋጌ መሰረት በሚሰጡት አስተያየት ላይ በመመስረት ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ ለታተሙት ሁሉም የጆርናል እትሞች የፕላጂያሪዝም ምርመራ ይካሄዳል.

## አንቀፅ ፱. የእያንዳንዱ ጆርናል ውጤቶች አመዘጋገብ

፩/. በውጫዊ ግምገማ ውስጥ የእያንዳንዱን ጆርናል እትም ዝርዝር ውጤቶች ለመቅዳት በማህበሩ፣ በሚኒስቴሩ ወይም በገምጋሚው የቀረበው ወጥ ቅጽ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

## Article 8. Assigning of Scores

1/. The Evaluator may set a further breakdown of the total points allotted to each criterion in accordance with the indicators to make the scoring process as objective as possible.

2/. The Evaluator is responsible for assigning scores under each criterion in the external evaluation and shall provide valid justifications under each instance to ensure that scores are not assigned mechanically or arbitrarily; these justifications would be reviewed when addressing any appeals.

3/. After selecting articles to be reviewed per issue, the Chair of the evaluators shall assign the articles for further evaluation by individual evaluators.

3/. Based on the remarks shown in 7.1, plagiarism checking will be conducted for all issues of the journal published in the last three years.

## Article 9. Separate Recording of Each Journal's Scores

1/. A uniform template supplied by the association, the Ministry, or Evaluator shall be used for separately recording each journal issue's detailed scores in the evaluation.

፪/. በእያንዳንዱ መመዘኛ መሰረት ለእያንዳንዱ ለተመረጠው ጽሁፍ የተሰጠው ነጥብ ይደመርና ለተገመገሙት የጆርናሉ ጽሁፎች ብዛት ይካፈላል፣ ለተገመገሙት ሁሉም ጽሁፎች የተገኘው አማካኝ ነጥብ እንደ ጆርናሉ ውጤት ይመዘገባል፣ ይህንን ተመሳሳይ የስሌት መርህ በመጠቀም የመጨረሻው ውጤት ይሰላል፣ አንድ ጆርናል በእያንዳንዱ መስፈርት የሚያገኘው አማካይ ነጥብ ይወሰዳል::

2/. Each selected article's score under each criterion will be summed up, divided by the number of the journal's articles reviewed, and the average recorded as the journal's score for all the articles assessed; the same principle will apply for consolidating the average score that a journal attains under each criterion.

**፫/. ለዕውቅና እና ለዳግም ዕውቅና ለማግኘት ብቁ ለመሆን የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ ውጤቶች**

(ሀ). ማንኛውም በውጭ የተገመገመ ጆርናል በሁሉም የግምገማ መስፈርቶች ከተገኘው ውጤት ቢያንስ ፷% ማግኘት አለበት::

(ለ). ለድጋሚ እውቅና የተገመገመ ጆርናል በሁሉም የግምገማ መስፈርቶች ከተገኘው ውጤት ቢያንስ ፸ ከመቶ ማግኘት አለበት::

(ሐ). የተገኘው ውጤት በአስርዮሽ ቁጥር የተገለጸ ከሆነ፣ ቅርብ ወደሚገኘው ሙሉ ቁጥር መጠጋጋት ይኖርበታል::

(መ) በተለያዩ ገምጋሚዎች ለተመሳሳይ ጆርናል ወይም ፅሑፍ በተሰጡት ውጤቶች መካከል የ፲፭ ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ልዩነት ካለ ጆርናሉ በሌሎች ብቁ ባለሙያዎች እንደገና ይገመገማል::

**3/. Minimum Scores Required to Qualify for Accreditation and Reaccreditation**

(A) Any externally evaluated journal for ***accreditation*** has to attain at least 60% of the scores earned under all of the evaluation criteria.

(B) A journal evaluated for ***re-accreditation*** has to achieve a minimum of 70% of the scores earned under all of the evaluation criteria.

(C) In case of decimal values, scores shall be rounded off to the nearest value.

(D) If there is a discrepancy of 15 points or more between the scores given by different evaluators for the same journal or article, the journal shall be re-evaluated by other qualified professionals.

**፬/. በጆርናል እትም የሚገመገሙ የጽሁፎች ብዛት**

4/. **Number of Articles per Journal Issue to be Reviewed**

ጆርናሎች የሚያስገመግሙት ዝቅተኛው የጽሁፎች ብዛት በሠንጠረዥ ፩ እንደተመላከተው በአመት በሚያዘጋጁት የህትመት ብዛት መሰረት መሆን አለበት:: እያንዳንዱ ጆርናል ቢያንስ በሁለት ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ይገመገማል::

**ሠንጠረዥ ፩: በየጆርናል - እትም የሚገመገሙ መጣጥፎች ብዛት**

| ተ.ቁ | ቋሚ እትም (በአመት) | የሚገመገመው ዝቅተኛው የጽሁፍ ብዛት |
|---|---|---|
| ፩. | አንድ | ፪ |
| ፪. | ሁለት | ፫ |
| ፫. | ሶስት | ፬ |
| ፬. | አራት | ፭ |

**አንቀጽ ፲. በእውቅና አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያሉ የቅደም-ተከተል ደረጃዎች**

**፩/ የማመልከቻ ግምገማ**

(ሀ). ጆርናሉ በመመሪያው ላይ በተመላከቱ የማመልከቻ መስፈርቶች ላይ ተመርኩዞ የተፈረመ የማመልከቻ ደብዳቤ እና ደጋፊ ሰነዶችን ያቀርባል::

(ለ). ሚኒስቴሩ ሁሉም አስፈላጊ መረጃዎች በማመልከቻው ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል::

The minimum number of articles to be reviewed for journals with various frequencies of publication shall be as per Table 1. Each journal shall be reviewed by a minimum of two qualified professionals.

**Table 1: Number of articles per Journal issue to be reviewed**

| SN | Regular issue per annum | Minimum number of articles to be reviewed |
|---|---|---|
| 1. | One | 2 |
| 2. | Two | 3 |
| 3. | Three | 4 |
| 4. | Four | 5 |

**Article 10. Steps in the Accreditation Process**

**1/ Application Review**

(A). Journals submit a signed application letter and supporting documents as outlined in the submission requirements.

(B). The Ministry verifies that all required information is included in the application.

**፪/ ግምገማ**

(ሀ). ብቁ የሆኑ ገምጋሚዎች በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ማመልከቻዎቹን ለመገምገም ይመደባሉ::

(ለ). ጆርናሎች የሚገመገሙት ሳይንሳዊ ጥራትን፣ የአርትዖት ፖሊሲዎችን፣ የአርታዒ ቦርድ መገለጫዎችን፣ አሰረጫጨትን እና ሌሎችንም በመመርኮዝ መሆን አለበት::

(ሐ). ሁሉም የቀረቡት ጆርናሎች ከግምገማው ሂደት በፊት የፀረ-ስርቆት ምርመራ ይደረግባቸዋል::

**፫/ ግብረ-መልስ**

(ሀ). ገምጋሚዎች ግኝቶቹን እና ውጤቶችን የሚገልጽ ረቂቅ ሪፖርት ያዘጋጃሉ::

(ለ). ገምጋሚዎች በግኝቶች ላይ ለመወያየት እና በውጤቶች ላይ መግባባት ላይ ለመድረስ ይገናኛሉ::

(ሐ). ገምጋሚዎቹ የመጨረሻ የግምገማ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ::

**4/ ዕውቅና ያገኙ ጆርናሎችን ለህዝብ ማሳወቅ**

(ሀ). ሚኒስቴሩ የግምገማ ሪፖርቶችን ይገመግማል እና የእውቅና ሁኔታን ይወስናል::

(ለ). እውቅና የተሰጠው ጆርናል ይፋዊ የውጤት ማሳወቂያ ይደርሰዋል:: እውቅና ያላገኘው ጆርናል ግን ለውሳኔው ከነምክንያቶቹ ይነገረዋል::

**2/ Evaluation**

(A) Qualified evaluators shall be assigned to assess the applications based on established criteria.

(B) Journals are evaluated on scholarly quality, editorial policies, editorial board profiles, and distribution practices, among others.

(C) All submitted journals undergo anti-plagiarism checking before the evaluation process.

**3/ Feedback**

(A). Evaluators prepare a draft report detailing the findings and scores

(B). Evaluators meet to discuss findings and reach a consensus on scores

(C) The evaluators submit a final evaluation report to the Ministry.

**4/ Publicize Accredited Journals**

(A) The Ministry reviews the evaluation reports and decides on accreditation status.

(B) Accredited journals receive official notification, while those not accredited are informed of the reasons for the decision.

## 5/. የቅሬታ አቀራረብ እና ይግባኝ አስተዳደር

### (ሀ) የቅሬታ አቀራረብ ሂደት

(i)_ እውቅና የተነፈጉ መጽሔቶች ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

(ii)_ ቅሬታው በተዘጋጀው የቅሬታ ጊዜ ውስጥ (የእውቅና ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ) መቅረብ አለበት።

(iii)_ ቅሬታው ከግምገማ ውጤቶች ጋር አለመግባባት የተፈጠረበትን ምክንያት የሚገልጽ መደበኛ ደብዳቤ ማካተት አለበት።

(iv)_ አሳታሚው ወይም ጆርናሉ ከስርቆት ጽሁፍ ጋር በተያያዙ በተወሰኑት ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

(v)_ ማመልከቻው የቅሬታውን ምክንያቶች በዝርዝር በመግለጽ በጽሁፍ መቅረብ አለበት።

(vi)_ ገለልተኛ ኮሚቴ ተሰይሞ ቅሬታውን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

### (ለ). ይግባኝን በተመለከተ

(i)_ ሚኒስቴሩ ይግባኝን የሚገመግም ገለልተኛ ኮሚቴ ያቋቁማል።

(ii)_ ኮሚቴው የቀረበውን ይግባኝ ከዋናው የግምገማ መስፈርት አንፃር ይገመግማል።

(iii)_ ኮሚቴው ወስኖ የይግባኙን ውጤት በተመለከተ ለጆርናሉ የጽሁፍ ምላሽ ይሰጣል።

## 5/. Grievance and Appeal Handling Mechanisms

### (A) **Grievance Process**

(i)_ Journals that have been denied accreditation may submit a grievance.

(ii)_Grievance must be submitted within the designated appeal period (within a month from the date of accreditation announcement).

(iii)_ The grievance must include a formal letter outlining the reasons for disagreement with the evaluation results.

(iv)_ The publisher or journal may forward grievance decisions related to plagiarism allegations.

(v)_ Grievances must be submitted in writing, detailing the grounds for the grievance.

(vi)_ A neutral committee shall be appointed and review the grievances and make a final determination.

### (B). Regarding Appeal

(i)_ A Ministry appoints a neutral committee to review appeals and grievances.

(ii)_ The committee assesses the submitted appeal against the original evaluation criteria.

(iii)_ The committee decides and provides a written response to the journal regarding the outcome of the appeal.

### (ሐ). ግልጽነት እና ግንኙነት

(i)_ ጆርናሉ ከእውቅና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በግምገማ መስፈርቶች እና ሂደቶች ላይ ማብራሪያ እንዲጠይቅ ይበረታታል።

(ii)_ ሁሉም ውሳኔዎች፣ አቤቱታዎችን እና ቅሬታዎችን ጨምሮ፣ በእውቅና አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ግልጽነትን ለመጠበቅ መመዝገብ አለባቸው።

### (C) Transparency and Communication

(i)_ Journals are encouraged to seek clarification on evaluation criteria and processes throughout the accreditation period.

(ii)_ All decisions, including appeals and grievances, shall be documented to maintain transparency in the accreditation process.

### አንቀጽ ፲፩. የጆርናል ደረጃ አሰጣጥ

፩/. ሚኒስቴሩ የግምገማውን አጠቃላይ ውጤት መሰረት በማድረግ የጆርናል ደረጃ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት አለበት።

፪/. በዚህ ስርዓት የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን ጆርናሎች ለማበረታታት እና ለመሸለም እንዲሁም በተመሳሳይ መስክ ውስጥ ባሉ ጆርናሎች መካከል ጤናማ ውድድርን ለማነሳሳት ያለመ ነው።

፫/. ይህ አሰራር ሲተገበር በጆርናሉ አጠቃላይ ነጥብ ላይ በመመስረት በሠንጠረዥ ፪ ላይ እንደተመላከተው ለጆርናሉ ደረጃ ይሰጣል፡-

**ሠንጠረዥ ፪፡ የጆርናል ደረጃ**

| ተ.ቁ. | ደረጃ (በፊደል) | የጆርናል ደረጃ | ጠቅላላ ነጥብ | ቁልፍ መስፈርት |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ሀ | እጅግ በጣም ጥሩ | ፹፭-፻ ነጥብ | በሁሉም ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ነጥብ ያመጣ |
| ፪ | ለ | በጣም ጥሩ | ፸-፹፬.፱ ነጥብ | በቁልፍ ጉዳዮች ከፍተኛ ነጥብ ያመጣ |

### Article 11. Journal Ranking

1/. The Ministry shall introduce a journal-ranking scheme based on the overall result of the external evaluation.

2/.The scheme aims to encourage and reward best-performing journals and inspire a healthy competition among journals within the same field.

3/. When applied, journals will be ranked in accordance with Table 2 based on the journal's total score:

**Table 2: Journal ranking**

| S. n. | Letter Grade | Journal rank | Total score earned | Key requirements |
|---|---|---|---|---|
| 1 | A. | Excellent | 85-100 pts | High scores in across all areas |
| 2 | B | Very Good | 70-84.9 pts | Strong performance core scholarly areas |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፫ | ሐ | ጥሩ | ፷-፷፱.፱ ነጥብ | ዝቅተኛውን ነጥብ ያሟላ (ለዕውቅና ብቻ) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | C | Good | 60-69.9 pts | Meets minimum standards (for accreditation only) |

፫/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፩.፪ የተገለጸው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በግምገማው ፷፱.፱ (ደረጃ ሐ) እና ከዚያ በታች ያመጣ የድጋሚ እውቅና አመልካች ጆርናል ውድቅ ይሆናል::

፬/. በዌብ ኦፍ ሳይንስ እና/ወይም ስኮፐስ ቋት ላይ የተመዘገበ እና ደረጃውን ያስጠበቀ ጆርናል ይህንን መመሪያ በመጠቀም መገምገም ሳያስፈልገው ከሀገራዊ እውቅና አሠጣጥ ሂደት ነፃ እንዲሆን ይደረጋል:: እንደዚህ ያለ ጆርናል እውቅና እንዳለው ተደርጎ በመውሰድ "እጅግ በጣም ጥሩ" ተብሎ እንዲመደብ ይደረጋል::

3/. Notwithstanding the provisions of Article 11.2 of this Directive, for re-accreditation, a journal that scores 69.9 and below (Grade C) shall be rejected.

4/. A journal that is exempted from the national accreditation process since it is indexed by Web of Science and/ or Scopus shall not be evaluated using this Directive as long as the journal continues to be indexed in the mentioned databases. Such journal shall be accepted automatically and ranked as "excellent".

## አንቀጽ ፲፪. የጆርናሎች ቋንቋ

፩/. ጆርናል እንግሊዝኛ እና/ወይም የሃገር ውስጥ ቋንቋዎችን ሊጠቀም ይችላል::

፪/. የጆርናል ጽሁፎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሁለት ቋንቋ ሊታተሙ ይችላሉ::

፫/. በሃገር ውስጥ ቋንቋዎች የሚታተም የምርምር ጆርናል በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፉ እና ሳይንሳዊ ጽሑፎችን ማካተት አለበት::

፬/. በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለሚታተሙ የምርምር ጆረናሎች ጥራትና የስርቆት ምርመራ ወይም ቁጥጥር ዝርዝር ስታንዳርድ እንዲዘጋጅ ይደረጋል::

## Article 12. Media of Journals

1/. A journal may use English and/or the local languages.

2/. Journal articles may be published in whole or in part in two languages.

3/. The research Journal publishing in local languages shall include abstracts and bibliographies in English language.

4/. A detailed standard shall be prepared for the quality and plagiarism checking or control of research Journals published in the Ethiopian languages.

## አንቀጽ ፲፫. የገምጋሚዎች አመራረጥ እና ኃላፊነት

### ፩/. የገምጋሚዎች የምርጫ መስፈርቶች

(ሀ). አንድ በገምጋሚነት የሚሳተፍ ባለሙያ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

(i). ቢያንስ ቢያንስ አምስት ጽሁፎች ወይም ፬፻ የሕትመት ነጥቦች ያለው የማስተርስ ዲግሪ በአለም አቀፍ ደረጃ በጆርናሎች (የዌብ ኦፍ ሳይንስ እና/ወይም ስኮፐስ) ላይ ያሳተመ፣

(ii). ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ኖሮት በአገር አቀፍ ደረጃ እውቅና በተሰጣቸው ጆርናሎች ቢያንስ ሰባት ጽሁፎች ያለው ወይም ፬፻፶ የሕትመት ነጥቦች ያለው፣

(iii). ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ኖሮት በአለም አቀፍ ደረጃ ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ እውቅና በተሰጣቸው ጆርናሎች ላይ ቢያንስ ስድስት ጽሁፎች ያለው ወይም ፬፻፳፭ የሕትመት ነጥቦች ያለው፣፣

(iv). የጆርናል ጽሑፎችን በማሳተም፣ በአርትዖት እና ግምገማ ስራዎች በሃገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡

(ለ). ገምጋሚው ቡድን የሚያሳትመው ጆርናል ውጭ የተውጣጣ የብዝሃ-ዘርፍ ባለሙያዎች ድብልቅ ቡድን መሆን አለበት፡፡

## Article 13. Selection and Responsibilities of Evaluators

### 1/. Criteria for Selection of Evaluators

(A) A professional participating as evaluator must meet the following criteria:

(i). A minimum qualification of a Master’s Degree with a minimum of five articles or 400 publication points in internationally indexed journals (Web of Science and/or Scopus)

(ii). A minimum qualification of a Master's Degree with a minimum of seven articles or 450 publication points in nationally accredited journals,

(iii). A minimum qualification of a Master’s Degree with a minimum of six articles or 425 publication points in both internationally indexed or nationally accredited journals,

(iv). It should include reviewers with national and international experience in publishing, editing, and reviewing journal articles.

(B)_ The review team should be a multidisciplinary team of experts from outside the publishing journal.

(ሐ). የገምጋሚ ቡድኑ ስብጥር ጆርናሉ የሚታተምባቸውን ዘርፎችን በአንድ ላይ በማጣመር ተቀራራቢ የዲሲፕሊን ዘርፎችን (ለምሳሌ፡ ማህበራዊ ሳይንስ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ፣ የጤና ሳይንስ፣ ወዘተ) እንዲወክል መደረግ አለበት::

(C)_ The composition of an evaluator is expected to represent the range of subject areas of the journals assigned to them by banding them together into interrelated disciplinary clusters (e.g., Social Sciences, Natural Sciences, Health Sciences, etc.).

## ፪/. የሥራ ጫና እና የገምጋሚው ተግባራት

## *2/. Workload and Tasks of the Evaluator*

(i)_ በግምገማ ሂደት ውስጥ ለገምጋሚዎች ግልጽ የስራ ክፍፍል መቀመጥ አለበት::

(i)_ A clear division of labor shall be maintained between the Evaluators in the evaluation process.

(ii)_ ማንኛውም ገምጋሚ በተመሳሳይ ጆርናል ላይ የታተሙ ከሁለት በላይ ጽሑፎችን መገምገም የለበትም::

(ii)_ No Evaluator shall assess more than two articles published in the same journal.

(iii)_ ከተመሳሳይ ጆርናል ለሚወጡት መጣጥፎች የተመደቡት ውጤቶች በጠቅላላ በተገመገሙት መጣጥፎች ብዛት መካፈል እና ለእያንዳንዱ ጆርናል በሚዘጋጁ አብነቶች ውስጥ በሁለቱ መመዘኛዎች የተመዘገቡ አማካኝ ውጤቶች መካፈል አለባቸው::

(iii)_ The scores assigned to the articles from the same journal should be added up and divided by the total number of articles assessed, and the average scores recorded under the two criteria in the templates to be prepared for each journal.

(iv)_ የግምገማ ውጤቶቹን ከማቅረብ በተጨማሪ፣ ገምጋሚው የመጽሔቱን ውስንነቶች፣ የታቀዱ መፍትሄዎች እና/ወይም ምክሮችን የሚገልጽ ሪፖርት ማካተት አለበት::

(iv)_ Apart from submitting the evaluation results, the Evaluator shall include a report stating the journal's limitations, proposed solutions, and/or recommendations.

## አንቀፅ ፲፬. የገምጋሚው የስነ-ምግባር ደንብ

## *Article 14. Code of Ethics for Evaluator*

የግምገማውን ሂደት ትክክለኛነት እና ግልፅነት ለማረጋገጥ ማንኛውም ገምጋሚ የሚከተሉትን የስነ-ምግባር መርሆዎች ማክበር አለበት፡-

To ensure integrity and transparency of the evaluation process, any evaluator shall observe the following ethical principles:

፩/. ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ ከማንኛውም ማህበር እሱ እንዲገመግም ከተመደበው ጆርናል ጋር የሚያያዝ የትኛውንም የጥቅም ግጭት በቅድሚያ የማሳወቅ፤

1/. Declare from the outset any conflict of interest arising from any formal association, during the last three years, with any of the journals one is assigned to evaluate;

፪/. በጆርናል ግምገማ ውስጥ በወቅቱ ስለተሰጣቸው ኃላፊነት ማንነታቸው እንዳይገለጽ የማድረግ፤

2/. Maintain anonymity concerning his current assignment in the evaluation of the journals;

፫/. በጆርናል የግምገማ ሂደት ውስጥ ገለልተኛነትን፣ ተጨባጭነትን እና ፍትሃዊነትን ማሳየት፤

3/. Maintain impartiality, objectivity, and fairness throughout the journal evaluation process;

፬/. ሚኒስቴሩ ለአመልካች፣ ለጆርናል አዘጋጆች ወይም ለሕዝብ እንደቅደም ተከተላቸው ምን አይነት መረጃ መለቀቅ እንደሚኖርበት ስለሚወስን ገምጋሚው የግምገማዉን ዉጤት ምስጢራዊነት መጠበቅ ይኖርበታል።

4/. Maintain the confidentiality of the results of his evaluations, as it is up to the Ministry to communicate to the applicant, journal Editors, or the public, respectively, what information it deems worth releasing;

## አንቀጽ ፲፭. የስርቆት እና የስነ-ምግባር ስታንዳርዶች

## Article 15. Plagiarism and Ethical Standards

### ፩/. የፀረ-ስርቆት ፍተሻ እና ጣሪያዎች

### 1/. Anti-Plagiarism Checking and Thresholds

**(ሀ). የፀረ-ስርቆት ማጣራት ዓላማ**

**(A). Purpose of Anti-Plagiarism Checking**

(i)_ የአካዳሚክ ሕትመትን ትክክለኛነት ለማስጠበቅ፣ ሁሉም የቀረቡት ጽሑፎች በግምገማው ሂደት መጀመሪያ ላይ ጥብቅ የፀረ-ስርቆት ፍተሻዎችን ማድረግ አለባቸው።

(i)_ To uphold the integrity of academic publishing, all submitted articles must undergo rigorous anti-plagiarism checks at the beginning of the evaluation process.

(ii)_ ይህ ሂደት የሃሳቦችን እና የምርምር ግኝቶችን ምንጭ እና ትክክለኛ ባህሪ ያረጋግጣል።

(ii)_ This process ensures originality and proper attribution of ideas and research findings.

**(ለ) የፀረ-ስርቆት የማጣራት ሂደት**

**(B) Anti-Plagiarism Checking Process**

(i)_ ጆርናል ሁሉንም የቀረቡ ጽሑፎችን ለመቃኘት ተዓማኒ የሆነ ጸረ-ስርቆት ሶፍትዌር መጠቀም አለበት።

(i)_ A Journal shall use credible anti-plagiarism software to scan all submitted articles.

(ii)_ ተመሳሳይነቱን ለማረጋገጥ ዘመኑ የደረሰበትን የላቀ የስርቆት መፈተሻ ቴክኖሎጂ ሶፍትዌርን (ለምሳሌ ተርንቲን) ስራ ላይ ይውላል።

(ii)_ Latest and most advance Anti-Plagiarism software (such as Turnitin) shall be employed to check the similarity.

(iii)_ የጆርናል ዋና አዘጋጅ ጆርናሉን በፀረ-ስርቆት ሶፍትዌሩ ከተሰራው ሪፖርት ጋር እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል።

(iii)_ Editors-in-Chief are required to *submit their journals along with a plagiarism report* generated by the anti-plagiarism software.

## (ሐ). የተመሳሳይነት ጣሪያ

## (C). Similarity Threshold

(i) ሚኒስቴሩ ጆርናሉን የፀረ-ስርቆት ሶፍትዌሩን በመጠቀም ዳግም ፍተሻ ማድረግ ይጠበቅበታል።

(i) The ministry is required to re-evaluate *the journals for plagiarism* by the anti-plagiarism software.

(ii) ለእውቅና እና ለዳግም እውቅና ተቀባይነት የሚኖረው ከፍተኛው የተመሳሳይነት ኢንዴክስ ፳% ነው።

(ii) A maximum similarity index of 20% is acceptable for accreditation and reaccreditation

(iii) የተመሳሳይነቱ ከዚህ ጣሪያ በላይ የሆነ ጆርናል መስፈርቱን እንደማያሟላ ተቆጥሮ ውድቅ ይደረጋል።

(iii) Journals exceeding this threshold shall be deemed non-compliant and be rejected

(iv) የተመሳሳይነት ግምገማው ከጆርናሉ ወሰን ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የባለሙያዎች ስብስብ ይካሄዳል።

(iv) A pool of experts relevant to the scope of a journal shall evaluate similarity results.

(v) ባለሙያዎቹ በፀረ-ስርቆት ፍተሻ ወቅት የመገለል መስፈርቶችን በኃላፊነት ይወስናሉ።

(v) The experts shall responsibly decide on the exclusion criteria during anti-plagiarism checking.

**፪/. ለጥሰቶች የተቀመጡ ቅጣቶች**

**2/. Penalties for Violations**

**(ሀ) የጽሁፍ ስርቆት ላይ ስለሚጣሉ ቅጣቶች በተመለከተ**

***(A). Consequences of Plagiarism***

(i). ከተቀመጠው መቁረጫ ነጥብ በላይ የጽሁፍ ስርቆት የተገኘበት ጆርናል ወዲያውኑ ውድቅ ይደረጋል::

(ii). ውሳኔው ምንም ይሁን ምን ጆርናሎች ስለ ተገኘው የጽሁፍ ስርቆት ውጤቶች ይነገራቸዋል::

(i). Journals identified with plagiarism exceeding the threshold shall be immediately rejected.

(ii). Journals shall be informed of the results of plagiarism, regardless of the decisions

**(ለ). ለከባድ ጥሰቶች የተቀመጡ ተጨማሪ ቅጣቶች**

**(B). Additional Penalties for Serious Violations**

የጽሁፍ ስርቆትን ጨምሮ በተደጋጋሚ (ለ፪ ጊዜ ያክል) በከባድ የስነ-ምግባር ጥሰቶች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ጆርናሎች ቢያንስ ለአንድ አመት ከግምገማ እና እውቅና ሂደት እንዳያመለክቱ ጊዜያዊ እገዳ ይጣልባቸዋል::

Journals found guilty of serious ethical violations repeatedly (for 2 times), including plagiarism practices, shall face a temporary ban from submitting to the journal for the evaluation and accreditation process for at least one evaluation year.

**(ሐ) የሰው ሰራሽ አስተውህሎት ተዛማጅ ድንጋጌዎች**

**(C) Artificial Intelligence (AI) - related provisions**

(i) ጆርናሉ በሰው ሰራሽ አስተውህሎት ቴክኖሎጂ የተፈጠረውን ማንኛውንም ይዘት በሃላፊነት ማረጋገጥ አለበት::

(ii) ሚኒስቴሩ ከኢ-ስነምግባራዊ የሰው ሰራሽ አስተውህሎት አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማሻሻል የሰው ሰራሽ አስተውህሎትን ሃላፊነት በተሞላበት መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል ስትራቴጂ ያዘጋጃል::

(i) The journal shall responsibly check any content created by the Artificial Intelligence (AI) technology.

(ii) The ministry shall issue a strategy for responsible use of AI to address issues related to the unethical use of Artificial Intelligence.

## አንቀጽ 16. በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ጉዳዮች

### ፩/. የጆርናሎች ስም ለውጥን በተመለከተ

(i) አንድ አሳታሚ በጆርናሉ ተገቢነት እና ወሰን ላይ በመመርኮዝ የሚያስለውጠው ምክንያት ሲኖር በማስረጃ ስሙን ሊለውጥ ይችላል።

(ii) ስሙን የሚቀይር ጆርናል የማስተካከያ ማስታወቂያ ከደጋፊ ሰነዶች ጋር የማተም ሃላፊነት አለበት።

(iii) በጆርናሉ ላይ ጉልህ የሆነ የስም ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ ከአለማቀፍ ስታንዳርድ ከተገቢው አካል አዲስ መለያ ቁጥር ማምጣት አለበት።

(iv) የጆርናሉ የመለያ መረጃዎች፣ እንደ የጆርናሉ ዲ.ኦ.አይ. ያሉ መረጃዎች እንደነበሩ ሆነው የሚቆዩ ሲሆን ጆርናሉን የሚመለከቱ የቀደሙት መለያዎች በሙሉ ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

### ፪/. የእውቅና ቆይታ

(i) የዕውቅና ጊዜው ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ይቆያል።

(ii) እውቅና በተሰጣቸው ጆርናሎች ላይ የታተሙ ጽሑፎች ጆርናሉ ዕውቅናውን ካገኘበት ዓመት ጀምሮ ለእውቅና ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

## Article 16. Exceptional Issues

### 1/. Journals' name change policy

(i) A journal can change its name with justification on the relevance and scope variation of a journal.

(ii) A journal that changes its name will be responsible for publishing a correction notice with supporting documentation

(iii) A significant name change should result in a new International Standard for Serial Numbers from the relevant body.

(iv) Citation information, such as the DOI for the journal, remains the same, and all previous citations to the journal remain valid.

### 2/. Accreditation Duration

(i) The accreditation award will stay valid for three consecutive years.

(ii) The articles published in the accredited journals will be valid as accredited since the year of the journal's accreditation.

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፲፯. መመሪያውን ስለማሻሻል

፩/. ይህ መመሪያ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በማንኛውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል።

፪/. ማንኛውም የመመሪያው ማሻሻያ ተፈጻሚ በሚሆንበት ወቅት ለጆርናል አሳታሚዎች በትክክል እንዲገለጽ ይደረጋል።

### አንቀጽ ፲፰. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ ከዚህ መመሪያ ጋር የማይጣጣሙ መመሪያዎች እንዲሁም ማናቸውም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ላይ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

፪/. ማንኛውም ድንጋጌ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት በነበሩ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### አንቀጽ ፲፱. ተጠያቂነት

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የጣሰ ማንኛውም ሰው በየትኛውም ደረጃ ያለ ፈፃሚም ሆነ አስፈፃሚ አካል አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

## PART FOUR

## MISCELANOUS PROVISIONS

### Article 17. Amendment of the Directive

1/. This Directive or any part thereof may be amended by the Ministry at any time.

2/. Any amendment of the Directive shall be duly communicated to the journal publishers before application.

### Article 18. Inapplicable Rules

1/ Directives that are not in conformity with this Directive, as well as any customary practices, shall not be applicable on matters provided for in this Directive.

2/. Any amendment shall not be applicable retroactively.

### Article 19. Accountability

Anyone who violates the provisions of this Directive shall be held accountable in accordance with the relevant laws of the country without any executive or executive branch at any level.

**አንቀጽ ፳. መመሪያው ስራ ላይ የሚውልበት ቀን**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስቴር ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

ጥቅምት፣ 2018

አዲስ አበባ

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

ሚኒስትር፣ የትምህርት ሚኒስቴር

**Article 20. Effective Date**

This directive shall enter into force upon the date it is registered with the Ministry of Justice and posted on the Website of the Ministry of Education.

October, 2025

Addis Ababa

Berhanu Nega (Professor)

Minister, Ministry of Education